Maahanmuuttovirasto
Migrationsverket
Finnish Immigration Service

# የመቀበያ ማእከል ደንበኛ - የክፍያ ካርዶች ላይ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፣ በዚህ ጊዜ ካርዶቹ ላይሰሩ ይችላሉ

በፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት የተሰጠ የቅድመ ክፍያ ካርድ ላላቸው ደንበኞች ሁሉ ምርመራዎች የሚደረጉ ሲሆን ይህም ምርመራ ለሁለቱም ማለትም ለአዲስም ሆነ ለነባር የካርድ ባለቤቶች ተፈጻሚነት ይኖረዋል። በሁሉም የባንክ ቁጥሮች እና የካርድ ባለቤቶች መደበኛ ምርመራ ይደርጋል። ምርመራው አውቶማቲክ ክንዉን ስለሆነ በበኩልዎ ለምርመራው ምንም ነገር ማድረግ አይጠበቅቦትም። የአውቶማቲክ ምርመራው ብዙውን ጊዜ በካርዱ ክንዉን ላይ ጉዳት አያስከትልም

ምርመራው ከተለመደው በላይ ማጣራት የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ እስኪጠናቀቅ ድረስ ካርድዎ እና ተጓዳኝ አካውንትዎ ከአገልግሎት ዉጪ ሆነው ይቆያሉ። ካርድዎ እና የባንክ ቁጥርዎ የማይሰሩ ከሆነ የመቀበያ ማእከልዎን ያነጋግሩ።

ካርድዎ እና የባንክ ቁጥርዎ የማይሰሩ ከሆነ የመቀበያ ማእከልዎን ያነጋግሩ።

## በፍተሻው ወቅት የመቀበያ ማእከሉ መሰረታዊ ፍላጎቶችዎን ያሟላልዎታል

ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት መሰረታዊ ፍላጎቶችዎን ለማሟላት ገንዘብ እና አመቺ ሁኔታ ከሌልዎት ከመቀበያ ማእከሉ አርዳታ፣ ለምሳሌ በምግብ እና በመድሃኒት መልክ ማግኘት ይችላሉ።

እባክዎን ያስተውሉ፣ ነገር ግን ፍተሻው ከወትሮው የረዘመ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ፣ ከመቀበያ ማእከሉ የሚሰጠዎት የገንዘብ ድጋፍ በኋላ ሊከፈልዎት የሚችለውን የመቀበያ ገንዘብ ልክ ሊያሳንስ ይችላል።

ምንም እንኳ ቅጥር ሰራተኛ ቢሆኑና ነገር ግን በምርመራው ምክንያት የቅድመ ክፍያ ካርድዎን መጠቀም የማይችሉ ከሆነ የእንግዳ መቀበያው ማእከል መሰረታዊ ፍላጎቶችዎን ሊያሟላ ይችላል። የተሰጠው የገንዘብ ድጋፍ ወደፊት ከሚከፈለዎ ደሞዝዎ ተመላሽ ሊደረግ ሲይችላል።

ምርመራው በሚካሄድበት ጊዜ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ስለማስጠበቅ ተጨማሪ መረጃ ከመቀበያ ማእከልዎ ማግኘት ይችላሉ።

## ምርመራዎቹ ለምን አስፈለጉ?

ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል በወጣው ህግ መሰረት፣ ለምሳሌ ባንክ ወይም የክፍያ ካርድ አቅራቢ ደንበኛውን ማወቅ አለበት። ይህ፣ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ፖለቲካዊ ተፅእኖ መፍጠር የሚችሉ (ፒ.ኢ.ፒ) ሰዎችን እና በአገር አቀፍ ወይም በአለም አቀፍ ድረጃ የኢኮኖሚ ማዕቀብ የተጣለባቸውን ሰዎች መለየትን ያካትታል።

ምርመራዎቹ ፒ.ኢ.ፒ እና የማዕቀብ የማጣናከርያ ምርመራዎች ናቸው። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በደነገገው ህግ መሰረት የመቀበያ ገንዘብ ተቀባዩ በፒ.ኢ.ፒ እና በማዕቀብ ማረጋገጫ ምርመራ ሂደት ላይ እስከሆነ ጊዜ ድረስ የመቀበያ ገንዘቡ በማንኛውም የመክፈያ ዘዴ ሊከፈለው አይችልም።

የምርመራው ሃላፊነት የካርድ አቅራቢው የኤንፉሴ (Enfuce) ነው። የማረጋገጫ ምርመራው በተለምዶ ከ1 እስከ 3 የስራ ቀናት ይፈጃል፣ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድም ይችላል።

ማስተካከያ 20. 3. 2025: የማስታወቂያውን ርዕስ በማስተካከል የአውቶማቲክ ማረጋገጫው  አብዛኛውን ጊዜ የካርዱን ተግባር እንደማይጎዳው አብራርቷል።